## የጋዜጠኛው ማስታወሻ? ወይስ የጋዜጠኛው ማረሳሻ?

ይህ አስተያየት በቅርቡ ከየአቅጣጫው የጎረፉ ቅጽል ስሞችን የተከናነበውን መጽሐፍ የሚዳስስ ነው። የመጽሐፉ ርዕስ የጋዜጠኛው ማስታወሻ የሚል ሲሆን ደራሲው በወያኔ የድል አጥቢያ ዋዜማ ከደርግ ካድሬነት ወደ ወያኔ ጎራ በመሸጋገር በፕሮፓጋንዳ አሰራጭነት ተቀላቅሎ ከወያኔ አዲስ አበባ መግባት በኋላ ደግሞ ያለምንም የሥራ ልምድ በአንድ ትልቅ የአስተዳደር መስሪያ ቤት የሥልጣን ቁንጮ ላይ ቁጢጥ ያለ ግለሰብን የህይወት ታሪክና የሥራ ገጠመኝ ምርጥ ምርጦቹን «ብቻ» የሚያንጸባርቅ መጽሐፍ ነው። ምርጥ ያልኩበት ምክንያት ደራሲው አቶ ተስፋዬ እጅግ በተዋበ የድርሰት ችሎታው ሲያሰኘው የግል ህይወቱን ገጠመኝ ዝርዝር አድርጎ ሲነግረን ሌላ ግዜ ደግሞ በሥራ ላይ ያጋጠሙትን እውነታዎች ቀንጨብ እያደረገ ሲያዋዛን መክረሙን ነው። በመጽሐፉ ቆይታ። የእናንተን አላውቅም እኔ ግን ይህን መጽሐፍ ጀምሬ እስከምጨርሰው ድረስ የበላሁትን እህልና የጠጣሁትን ውሃ ቀርቶ የተነፈስኩት አየር ምን እንደሆነ አጥርቼ አላወቅሁትም። ቢያንስ በሦስት ሃሳቦች ክፉኛ ተወጥሬ ነበር። አንድ ሁለት ብዬ ከመዘርዘሬ በፊት ግን የደራሲውን የሥነ-ጽሁፍ ችሎታ ማድነቄን ሳልገልጽ ማለፍ አልፈልግም።

መጽሐፉን በማነብበት ወቅት በተስፋና በጉጉት የወጠረኝ አንደኛው ነገር፤ የለም ይህ ሰው ወደ መጽሐፉ ውስጠኛ ምዕራፉት ስንገባ ረቀቅ ጠለቅ ያሉ ምሥጢራትን ያካፍለንና ያለ ፈው አለፈ ለወደፊቱ የሃገራችንን ህልውና ሌለው ቢቀር ወደ ባሰ አዘቅት ከመግባት ሊያድን የሚችል እውነታውን ፍርጥርጥ አድርጎ ያጫውተናል ስል፤ እንዲያው ጠላታችሁ የውሃ ሽታ ይሁን «ብዙ ምሥጢሮችን አውቅ ነበር» እያለ ምራቅ ከማስዋጥ በስተቀር መቼም ምንም፤ ብንርቅ ምንም ብንሰደድ፤ ያልተሰደደውም ደግሞ በዝምታ መሸበቡ እንደ አላዋቂ ቢያስቆጥረውም፤ የሚታወቁትንና የሚጠረጠሩትን በወሬ የተናፈሱትን ያረጁ ጉዳያች እንደ አዲስ ሸክላ ጥዶ ሲያስሟሸን ከረመ። የሚደንቀኝ ነገር በየድኅረ ገጹ ላይ ፥«Explosive!!!» እንዲያው ሾላ በድፍን የሆነ አስተያየት አንብበናል።

ደራሲው አንዳንድ አስቂኝ የሆኑ ገጠመኞችን እንዳለ መተረክ መቻሉና አንባቢን በንዴት ከመቃጠል ወደ አስቂኝ ገጠመኝ በቀላሉ የማመላለስ ችሎታው አስደናቂ ነው። እናም በብዙ ገጠመኞች ከት ብዬ የኮረኮሩኝን ያህል በውድቅት ሌሊት ስቄያለሁ። የመጽሐፉን ማለቅ የሚያበስረውን የመጨረሻውን ገጽ ሳጥፍ ግን ቁጭት፤ ንዴት፤ ስላቅ፤ ምጸት የተባሉት ክፉ ክፉ ሜንጦዎች እጅግ አድርገው ኮረኮሩኝና በብዙ ዐይነት ስሜት የተጀቦነ ሣቄን ለረጅም ግዜ ለቀቅኩት። ማሽላ እያረረ ይስቃል ይሉ የለ? ሣቁን ሳበቃ ግን የወረረኝ ሃዘንና ፍርሃት ነው።
ይኸውም መጽሐፉን ባነበብኩበት ሰዓት ወጥሮ ወደያዘኝ ሁለተኛ ስሜት አሸጋገረኝ ማለት ነው።

ወያኔ በማን አለብኝነት የዕውር ድንብሩንና የንቀቱን ሃገሪቱን ወደ ጥፋት ህዝቧን ደግሞ ወደ ዘለዓለማዊ ውድቀት እየወሰደ መሆኑን ይህ ጉዳትም በቀላሉ ሊጠፉ የማይችል የትውልድ ጠባሳ እየተወ መሆኑን የሚያስገነዝቡ ጠቋሚዎች በመጽሐፉ በእርግጠኛነት ተጠቅሰው ይገኛሉ። እንዲያው በጥቂቱ። ይኸ እኩይ ስልት ወደተግባር እየተለወጠ፤ የወያኔ የሥልጣን እድሜ እየረዘመ በመጣ ቁጥር በአንዳች መርዝ በጅምላ የተፈጀ

የባህር አሣ ቀስ በቀስ ወደላይ እየተንሳፈፈ እንደሚሸትና ጠረኑ እንደሚለወጥ አካባቢውን ውኃውን እንደሚበክል ሁሉ የወያኔ እኩይ ድርጊትም እንደዚሁ እየሆነ ነው። እውነታው ይኸ ሆኖ ሳለ «የጋዜጠኛው ማስታወሻም» አንዳንድ በጥርጣሬ የሚታወቁ ተግባራት እውን መሆናቸውን በጅምላው፤ በደፈናው አረጋገጠልን እንጂ «ዜጋ» እያለ ለተናገረለት ሃገር ህልውና እንደተከበረ መቆየት የሚያበረክት አስተዋጽዖ፤ ክፉ ሠሪዎችን ወደ ፍርድ የሚያመጣ፤ የወደፊት እቅዳቸውን የሚያጋልጥ ተጨባጭ ንድፍ፤ሃገር የማፍረስ፤ ድሃውን ሕዝብ የመመዝበር ምኞታቸው እንዳይሰምር የሚያኮላሽ የሚያከሽፍ መንገድ አልነገረንም። ይኸም ከፍተኛ የሆነ ቁጭትና ሃዘን ላይ ጥሎኛል።

አይ አንቺ ሃገር ሁልጊዜ የበደሉሽ ሥራቸው የማይገለጥበት፤ ፍትህ ርትዕ የማይሰፍንበት ሃገር ትሆኚ? ብዬ እንዳዝን አድርጎኛል። በኔ አመለካከት የዚህ ከፍተኛ ሥልጣን ላይ የነበረ ሰው ሥራውን ትቶ «ሃገሬ» የሚላትን  ሃገር ትቶ፤ ሕዝቤ የሚለውን ቅዬ የሚ ናፍቀውን ቦታ ትቶ መሰደድ ልዩ ለሆነ ተልዕኮ፤ ብዙዎችን ከህሊና ስደት፤ ከአካል ስደት የሚያድን፤ ግፈኞችን ለፍርድ የሚያቀርብ የሚያንቀጠቅጥ፤ ወደፊት ለሥልጣን የሚታጩትን የሚያስተምር ይሆናል፤ ወይም መሆን ነበረበት ብዬ ገምቼ ነበር። አልሆነም።

«ለሠራተኛ ደሞዙ አይከለከለውም» የሚባል አባባል አለና፤ ለዚህም ደራሲና መጽሐፍ ያላቸውን ስኬታዊ ውጤት መንፈግ አይገባም። በዚህ አጋጣሚ መጽሐፉ በኢንተርኔት መሰራጨቱን አጥብቄ እቃወማለሁ። ለምን ቢባል ከሕግ ውጭ የሆነ ሥራ በማንም ተሠራ በማንም «ሕገ ወጥ» ከመሆን አይድንም። ሃገር ዓቀፍ፤ ዓለም አቀፍ የሆኑ የኮፒ ጥበቃ ግዴታዎችን ማክበር የማናችንም ግዴታ ይመስለኛል። እንግዲህ በለስ ቀንቶት ቦታውን ይዞ ከዚያ ደግሞ የሃገሩ ነገር የሚገደውን  ኢትዮጵያዊ  ሁሉ በሚያማልል የአጻጻፍ ስልት አሳምኖ መክበር ከቻለ ይሁንለት። መቼስ የኢትዮጵያ አምላክ ይፋረደው እንጂ ሌላ ምን ይባላል?

አሳሳቢው ነገር የእሱ መጽሐፍ ጽፎ መክበር ሳይሆን ለኢትዮጵያ ተቆርቋሪ ነኝ የሚለው በሆነ ባልሆነው ሃሳቡ ሲባክን መጠየቅ ያለባቸው ፍሬ ነገሮች ለጥያቄ ሳይቀርቡ፤ እንዲሁ በእፍታ በእፍታው ንፋስ  እንደሚያባክነው የጤፍ  እብቅ ስንባክን ሃገራችንና ድሃ ሕዝቧን ለችግራቸው ሳንደርስ መቅረታችን ነው። ታዲያ በዘመናችን በሥልጣን ኮርቻ ላይ የሚቆናጠ ጡትም ግለሰቦች የመጀመሪያ የእውቀት ፋና አድርገው የሚይዙት እንዲህ ያለውን መመሪያ ነው። በዚህም ይመስለኛል ያለምንም ማወላወል በርካታ መረጃዎችን አካትቶ ወቅቱን ጠብቆ መጻፍ ሲገባው እንደዋዛ ከዓመታት በኋላ መውጣቱ ነው።  አዬ የዋሁ በሬ! ቀንበርን የመሰለ ከባድ ነገር በአንገቱ ሊጫን፤ ስለትን የመሰለ ከባድ ነገር በአንገቱ ሊያልፍ መሆኑን ስለማይረዳ አሞሌ መሰጠቱን ብቻ እያየ፤ ከአሞሌው ፍቅር የተነሳ ልጋጉን ሲያላግግ ጭራሽ በታማኝነት ሲለሳለስ ይታያል። እናም መጽሐፉን ስጨርስ የተሰማኝ ስሜት ይህ ነው።ምነው ጃል! ምን ያህል ነው  የኢትዮጵያ ሕዝብ ትዝብት ላይ የወደቀው? ምንም የማይገባን እንዲያው ጨርሶ የደነዘዘን አሞሌ የቀመሰ በሬ ሆነን ተገምተናልና አልኩኝ? ለምን ቢባል ሁሉ ካለፈ በኋላ የተነገረ ክስተት ታሪክ ሆኖ መቀመጥ እንጂ ቅን ፍርድን  ለማምጣት ምን አቅም አለው?

ይህ ደግሞ ወደ ሶሥተኛው የሃሳብ መዘውር አሸጋገረኝ።

መጽሐፉ «የጋዜጠኛው ማስታወሻ» በሚል ከተሰየመ ማስታወሻው ላይ የነበሩት እውነ
ታዎች በሙሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዜግነት መብቱ ድርጊቶቹ በተከሰቱበት ወቅት ሊያው
ቃቸው የሚገባቸው የህቅ ሰነዶች ናቸው እናም ለባለንብረቱ ሕዝብ ከምስጋና ጋር  መመለስ
ነበረበት እንጂ የጆፌ አሞራ መንጋ እንደተጫወተበት የሞተ ከብት ዝንጥልጥሉ መው
ጣት አልነበረበትም።  ይህንን አስቀድመን እንድንዘጋጅበት ደራሲው በገጽ 6  ላይ
«የሙያውን ሥነ-ምግባር ለመጠበቅ ስል ያላተምኳቸው መረጃዎች በጣም ጥቂት አይ
ደሉም» በማለት የተሰጠንን «ተመስገን» ብለን እንድንቀበል ያስጠነቅቀናል። ለመሆኑ የሃገር
ህልውና ዐመጸኛ የጎርፍ ውሃ እንደሚሸረሽረው ባለቤት እንደሌለው መሬት ሳይመለስ
እየተጠረገ እየተወሰደ ምን ዓይነት የሙያ ክብር ነው የሚጠበቀው? እንግዲያው እንዲ
ያው ለመሆኑ ሃገር ስትኖር አይደለምን የተለያዩ የሙያ ክብሮች ተጠብቀው ሊኖሩ
የሚችሉት? እንዴት ያለ ቀልድ ነው? ከዚሁም ሃሳብ ዙሪያ ሳንወጣ፤ ወያኔ ኢትዮጵያንና
የኢትዮጵያን  ሕዝብ  በድሏል/በድለዋል፤ እንጂ በድለናል! የሚል ሃላፊነት ውስጥ የሚያስገ
ባውን አባባል ሁሉ በወረንጦ ሲለቅም እንደዋለ ለመገንዘብ አያዳግትም። ምናልባት ይኸ ምክ
ንያት ይሆን መጽሐፉ ለብዙ ዓመት ሳይወጣ ያቆየው? የሚል ጥያቄ ቢነሳም አግባብ  ያለው
ይመስላል።

ሌላው ሳልጠቅሰው የማላልፈው ነገር ምንም እንኳን ተአማኒነት ባለው መልኩ ደራሲው
በወያኔ የፖለቲካ ርእዮት የማይስማማ መሆኑን ቢያስረዳንም የመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች ላይ
ራሱን የማዳን፤ ወይም የመከላከል ጥድፊያ የያዘው አስመስሎ ማቅረቡ ከዚህ ትረካ
ጀርባ ያለ እውነተኛ ታሪክ ምን ይሆን ብሎ መጠየቅ ነገሮችን በጥልቅ መመርመር ያለበት
የማንኛውም አንባቢ ተግባር ይመስለኛል። አልበደልኩም ይሆን? ግን አልበደልኩም
ሌላ ነገር ነው ሌላው ሲበድል አጋዥ መሆን ደግሞ ከፍርድ አያስመልጥም። ለዚህም
አስረጂው  አንዳንድ ቦታ የሃሳብ ግጭቶችና ትርምሶች ይታያሉ። በዚህም ምክንያት
በአንዳንድ ቦታ ላይም ወያኔ ውስጥ እንዳልነበረ አርቆ ይናገርና በሌሎች ቦታዎች ደግሞ
ጭርሱኑ «የኔዎቹ» እያለ ጉያው ሲያስገባቸው እናገኛለን። ይኸ ወጥ ያልያዘ ትረካው በኔ
ግምት መደበቅ የፈለገውን ነገር ሁሉ በመልካም ወንፊት እየደጋገም እንዳሳለፈው
ግልጽ አድርጎ የሚያስቀምጥ ነው። እንዲያውም «እንደ መግቢያ» ላይ እንደተናገረው
በመቶ የሚቆጠሩ ገጾች ቆርጦ የጣለው እነዚህንና የመሳሰሉትን ቀብሮ ለማስቀረት
ይመስላል። ለምን?

እንግዲህ ከሞላ ጎደል እኔ ስለመጽሐፉ ያለኝ አስተያየት ይኸ ነው። ምናልባት አቶ
ተስፋዬ በሥልጣን በነበረበት ጊዜ በሠራቸው ነገሮች ሁሉ ተጸጽቶ ወደ መልካም ምግባር
ይመለስ ይሆን? ተስፋ መቁረጥ አይገባም። ግን ደግሞ ተስፈኛ ሆኖም ዝም ማለት
አይገባም። እንዲህ ያለው በደል ሥርየት የሚያገኘው ራስን ከሕዝብ ጉልበት በታች ዝቅ
በማድረግ የበደሉትን ያህል ሠርተው ሲገኙ ብቻ ነው እንጂ በቃላት የተዋበ ድርሰት
ስለተጻፈም አይደለም። አለበለዚያ ዛሬ ተስተባበለም አልተስተባበለም ጊዜው ይርዘም
እንጂ  የፍርድ ቀን በግልም ይሁን በአደባባይ መምጣቱ የት ይቀራል?

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባረክ!